# መመሪያ ቁጥር.06./2010

## ልውጥ ሕያዋን ላይ በሚደረጉ ማናቸውም እንቅስቃሴዎች በተያያዘ ሊደርስ የሚችል ጠንቅ መቋቋሚያ የአሰራር ሥርዓት መመሪያ

ከልውጥ ሕያዋን እንቅስቃሴዎች በተያያዘ ሊደርሱ የሚችሉትን ድንገተኛ አደጋዎችን ለመከላከል የሚያስችል የጠንቅ መቋቋም አሰራር ሥርዓት መዘርጋት በማስፈለጉ፣

የአካባቢ፣ የደን እና የአየር ንብረት ለውጥ ሚኒስቴር ስለደሕንነት ሕይወት በወጣው አዋጅ ቁጥር 655/2001 (በአዋጅ ቁጥር 896/2007 እንደተሻሻለው) አንቀጽ 25 መሠረት ይህን መመሪያ አውጥቷል፡፡

## ክፍል አንድ
## ጠቅላላ

### 1. አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ "ከልውጥ ሕያዋን እንቅስቃሴ ጋራ የተያያዘ ጠንቅን የመቋቋሚያ የአተገባበር ሥርዓት ለመዘርጋት የተዘጋጀ መመሪያ ቁጥር 06/2010" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

### 2. የተፈፃሚነት ወሰን

(1) ይህ መመሪያ ለተጤነ እና ላልተጤነ ልቀት፤ ልውጥ ሕያዋን ለመሥራት፣ ለማስተማሪያነት፣ ለምርምር፣ ከውጪ ለማስመጣት፣ ወደ ውጪ ለመላክ፣ በትራንዚት ለማስተላለፍ፣ በዝግ ሁኔታ ለማምረት፣ ለማከማቸት፣ ለማጓጓዝ፣ በጥሬ ዕቃነት ለማዋል እና በገበያ ላይ በማዋል ጊዜ ሊፈጥር በሚችለው ጠንቅ ላይ ተፈፃሚነት ይኖራዋል፡፡

(2) በዚህ መመሪያ በሌላ ሁኔታ ካልተገለጸ በስተቀር ካልተጤነ ልቀት የሚመነጩ ጠንቆች ያሚከተሉትን ያጠቃልላል፤

ሀ/ በማከማቸት ወይም በማጓጓዝ ወቅት የሚንጠባጠቡ፣

ለ/ በሰዎች ስህተት የሚለቀቁ፣

Ministry of Environment, Forest and Climate Change

ሐ/ ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት የሚለቀቁ

**ክፍል ሁለት**

3. **ከማንኛውም እንቅስቃሴ የሚመነጩ ጠንቆችን የመቋቋሚያ ምላሽ**

(1) ማንኛውንም ፍቃድ ጥያቄ ሲቀርብ ሚኒስቴሩ ፍቃድ ከመስጠቱ በፊት ጥያቄው የሚከተሉትን መረጃዎች ማካተቱትን ማረጋገጥ ይኖርበታል፡፡

ሀ/ ደህንነትን ለማረጋገጥ የሚወሰዱ እርምጃዎች መረጃ እና የአተገባበር ስልትን ያጠቃለለ የአደጋ መቋቋሚያ ጊዜ እቅድን ማዘጋጀት እና

ለ/ በእንቅስቃሴው ጉዳት ሊደርስበት የሚችል ሰው/ሰዎች ቢኖሩ መረጃ የሚያገኙበት ዕቅድ መዘጋጀቱን ማረጋገጥ ይኖርበታል፡፡

4. **የድንገተኛ አደጋ መከላከል ግብረ ሃይል**

(1) ማንኛውም የልውጥ ሕያው እንቅስቃሴ ሲደረግ የሚያጋጥም ድንገተኛ አደጋን ለመቋቋም እንዲቻል የአደጋ መከላከል ግብረ ሀይል ሚኒስቴሩ ይሰይማል፡፡

(2) ሚኒስቴሩ የድንገተኛ አደጋ መከላከል ግብረ ሀይል ሲቀመንበርን፣ ጸሐፊንና አባላትን የድንገተኛ አደጋን የመቋቋሚያ እርምጃ መውሰድ አቅም ካላቸው ተቋማት መካከል ይሰይማል፡፡

(3) የድንገተኛ አደጋ መከላከል ግብረ ሀይል ኃላፊነቶችና ተግባራት ከዚህ በታች የተዘረዘሩት ናቸው፤

ሀ/ ብሔራዊ የአደጋ መቋቋሚያ እቅድን ማዘጋጀት፣ ሲያስፈልግ መተግበርና በየጊዜው ማሻሻል፤

ለ/ ማንኛውም ከልውጥ ሕያው እንቅስቃሴ የሚደርስ ያልተጤነ ልቀት መከሰቱን ለመለየትና ለመዘገብ የሚያስችሉ ተገቢ ስርዓቶችን መዘርጋት፤

ሐ/ ከልውጥ ሕያዋን ያልተጤነ ልቀት ሊመጣ የሚችለውን በሰው ወይም በእንስሳት ጤንነትና በአካባቢ የሚደርስ አደጋን ለመከላከል የሚያስችል ፈጣን የመቋቋሚያ ስልት ምንጊዜም ዝግጁ መሆኑን ማረጋገጥ፤

መ/ የልውጥ ሕያዋን ያልተጤነ ልቀት በሚያጋጥምበት ጊዜ በሰው ወይም በእንስሳት ጤንነት እና በአካባቢ ጉዳት ሳይደርስ ለውጥ ሕያውን ለማስወገድ በቂ ዝግጅት ምንጊዜም መኖሩን ማረጋገጥ፤

ሠ/ ወጪዎችን ለማስመለስና ካሳን ለማስከፈል እንዲያግዝ የአደጋ መቋቋሚያ እርምጃ በሚወሰድበት ጊዜ የሚደርሱ ወጪዎችን በተሟላና በትክክለኛ መንገድ መመዝገባቸውን ማረጋገጥ፤